- ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፣
- በታላቁ የኢትዮጵያ ታሪክ ምሁር በነበሩት በፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ የ፴ ቀን የመታሰቢያ ጸሎት ላይ የተገኛችሁ ክቡራትና ክቡራን እንግዶች፣
- የፕሮፌሰር ቤተሰቦች ጓደኞች፣

ከሁሉ አስቀድሜ ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የቀድሞ ተማሪዎቻቸው መካከል ስለፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ያለኝን ትዝታ በዚህ የጸሎት ሥነ ሥርዓት ላይ እንድገልጽ እድል በማግኘቴ የላቀ ክብር የተሰማኝ መሆኑን እገልጻለሁ።

ፕሮፌሰር ሥርግውን በመምህርነታቸውና በሌሎች አጋጣሚዎች ላውቃቸው ችያለሁ። በመጀመሪያ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለሁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መምህሬ ነበሩ። ፕሮፌሰር ሥርግው በሳምንት ሁለት ቀን ስድስት ኪሎ የአ. አ. ዩኒቨርስቲ ግቢ ሲያስተምሩን ክፍል ገብተው የትምህርቱ ክፍል ጊዜ እስኪይልቅ ድረስ ሌላ ሀሳብ ሳይቀላቅሉበት ለትምህርት ብቻ ያውሉት እንደነብር አስታውሳለሁ።

ፕሮፌሰር ሥርግው ጥብቅ መምህር ስለነበሩ ከክፍል የሚዘገይ ሆነ የሚቀር ተማሪ አልነበረም። እሳቸውም ለደቂቃ እንኳ አይዘገዩም ነበር።

ትምህርቱን ይሰጡ የነበረው አንድ ወጥ የሆነ የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ የውጭ ሀገር ምሁራን የጻፏቸውን መጻሕፍትና የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት የጻፏቸውን የብራና መጻሕፍት ያስነብቡንና ስለመጻሕፍቱም አስተያየት እንድንሰጥ ያደርጉን ነበር።

በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሚሰጠውን ትምህርት አጠናቅቄ በዛምቢያ የአሳታሚነት ሙያ ከተከታተልኩ በኋላ በ፲፱፻፷፪ ዓ. ም. የትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅትን እንዳቋቁም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በኃላፊነት ስለመደቡኝ እኔም ድርጅቱን ለማቋቋም መጀመሪያ ካማከርኳቸውና ሀሳቡን ከደገፉት ጥቂት ሰዎች አንዱ ፕሮፌሰር ሥርግው ነበሩ።

ስለማሳተሚያው ድርጅት ዓላማ ለፕሮፌሰር ስገልጽላቸው በጽሞና ካደመጡኝ በኋላ ድርጅቱ ለቤተ ክርስቲያናችን አስፈላጊና ጠቃሚ መሆኑን ገልጸውልኝ እቅዱንም ሥራ ላይ እንደማውል በእኔ ላይ እምነት እንደነበራቸው፣ እሳቸውም ከጐኔ ሆነው አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት እንደሚያበረታቱኝ ገለጹልኝ። እንደውም "የአራት ኪሎን የቤተ ክህነት ሕንፃዎች የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍት መሸጫዎች እናደርጋቸዋለን" በማለት የማይበርድ ሞራል ሰጥተውኝ እንደነበር አይረሳኝም። የማሳተሚያውም ድርጅት በ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ሲቋቋም ፕሮፌሰር ሥርግው ነፃ አገልግሎት ይሰጡ ከነበሩት የመጀመሪያው የቦርድ አባላት አንዱ ነበሩ።

ቦርዱ በሚያደርገው ስብሰባ ላይ ውይይት ሲካሄድ ፕሮፌሰር የሰውን ሀሳብ በጽሞና ማዳመጣቸው፣ ሳይቸኩሉ በጥንቃቄ ገንቢ ሀሳቦችን ያፈልቁ እንደነበረ ትዝ ይለኛል። ፕሮፌሰር ሥርግውና እንደሳቸው ለቤተክርስቲያናችን ቅን አሳቢዎች ድጋፍ ባይሰጡ ኖሮ ዛሬ ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያናችንን ጥንታዊ መጻሕፍት በማሳተም ላይ የሚገኘው ትንሣኤ የማሳተሚያ ድርጅት በወቅቱ ባልተቋቋመ ነበር።

ፕሮፌሰር ሥርግው ቀደም ሲል የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪ የነበሩ በመሆናቸው የሀገራችንንና የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክ፣ እምነት ባህል ይወዱና ያከብሩ ነበር። ይህንኑ በአዲሱ ትውልድ ዘንድ ለማስተዋወቅና ለትውልድ ለማስተላለፍ እድሜያቸውን በሙሉ ጥረት አድርገዋል።

የቤተ ክርስቲያናችንን ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት ለትውልድ ለማቆየት በደርግ ዘመን የባህል ሚኒስቴር የወረሰውን የማይክሮ ፊልምን ድርጅት ያቋቋሙት እሳቸው ነበሩ። ፲፬ ቮሊዩም የሆነውን የቤተ ክርስቲያናችንን መዝገበ ቃላት የጻፉትም ፕሮፌሰር ብቻ ነበሩ። እንዲሁም ባወጧቸውና ባዘጋጇቸው ጽሑፎች ሁሉ የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክና እምነት ለማጉላት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።

ከዚህ የተነሳ የቤተ ክርስቲያናችን ሁለተኛ ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከልብ ይወዷቸው ነበር፣ የፕሮፌሰርና የቅዱስነታቸው ግንኙነት የአባትና የልጅ ግንኙነት ዐይነት ነበር።

ፕሮፌሰር ለቤተ ክርስቲያናችን እምነት ባህልና ታሪክ የነበራቸውን ከበሬታና ጠንካራ እምነት ይበልጥ የሚያጐላ መሆኑን የሚያመለክት ተማሪያቸው በነበርኩበት ጊዜ የደረሰውን ሁኔታ በዚህ አጋጣሚ መጥቀስ እወዳለሁ። አንድ ቀን ስለ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ሲያስተምሩ አፄ አምደ ጽዮን (፲፰፻፲፬ - ፲፰፹፩ ዓ. ም.) ምንም እንኳ ለቤተ ክርስቲያናችን ዕድገትና መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ቢታወቅም፣ በመጀመሪያው የግዛት ዘመናቸው ከክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ውጭ ብዙ ዕቁባቶች የነበሯቸው ከመሆኑም ሌላ የእንጀራ እናቶቻቸውን ሳይቀር በማግባታቸው በወቅቱ ታዋቂ የነበሩት የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች /መነኮሳት/ ሊቃውንት ከየቦታው ተሰብስበው ከአስነዋሪ ድርጊታቸው እንዲያቆሙ ቢመክሯቸው እምቢ በማለታቸው አባ አኖሬዎስ የተባሉ እንዳውገዟቸው፣ ከዚህ የተነሳ አፄ አምደ ጽዮን አባ አኖሬዎስን ጀርባቸው እስኪደማ በአደባባይ እንዳስገረፏቸውና የአባ አኖሬዎስ ደምም እሳት ሆኖ የንጉሡ ከተማ የነበረችውን ተጉለትን ማቃጠሉን ነገሩን።

እኔም እጄን አውጥቼ “ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?” ስላቸው ያልጠበቁት ዓይነት ጥያቄ ስለሆነባቸው ሊሆን የማይችልበትን ምክንያት እንድነግራቸው ጥያቄዬን በጥያቄ መለሱት። እኔም ያልጠበቅሁት ዓይነት መልስ በመሆኑ ደነገጥኩ። ፕሮፌሰር እዙህ መልስ ላይ ብቻ አላቆሙም ነበር። በአውሮፓ የተማሩ በመሆናቸው ስለአውሮፓ ስልጣኔ ያውቁ ስለነበረ የምዕራባውያን የስልጣኔያቸው መሠረት የአምልኮ ባዕዳቸውና ተረቶቻቸው መሆናቸውን ነገሩን። እኛም በባህላችን፣ በታሪካችንና በእምነታችን መኩራት እንዳለብን በአጽንኦት አስተማሩን። ፕሮፌሰር ትዝ ባሉኝ ቁጥር አብሮ ትዝ የሚለኝ ይህ አጋጣሚ ነው።

የፕሮፌሰር ሕይወት ማለፉንና ሥርዓተ ቀብራቸው በጀርመን መፈጸሙን ከግል ጋዜጣ ሳነብ በጣም አዘንኩ። በዕለቱ ለማውቃቸውና ላገኘኋቸው ሁሉ ይህንን ስነግራቸው ዋልኩ፣ እቤት በስም ለምታውቃቸው ባለቤቴና ለልጆቼም ነገርኳቸው። ልጆቼ ፕሮፌሰርን ስለማያውቁ ማንነታቸውን ሲጠይቁኝ፣ በሰጠኋቸው መልስ እኔ የተማርኩበት የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የቀድሞ ተማሪ እንደነበሩ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ምሁርም ከመጀመሪያዎቹ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኢትዮጵያውያን መምህራን አንዱ እንደነበሩ፣ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲይን ታሪክ ብዙ ጽሑፎችን ያበረከቱና ትንሣኤ የማሳተሚያ ድርጅትን ሳቋቁም የረዱኝና መምህሬም እንደነበሩ፣ የደርግን የፖለቲካ ሥርአት በመጥላታቸው እንደ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ከእናት ሀገራቸው የተሰደዱ መሆናቸውን ነገርኳቸው። ትልቋ ልጄ የኔን ስሜት የተጋራች በመሆኑ የዛሬው የፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ የ፴ ቀን መታሰቢያ መከበሩን የሚገልጸውን ማስታወቂያ በሳምንታዊ ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ስታይ አምጥታ ከነፎቶግራፉቸው አሳየችኝ።

ፕሮፌሰር ሥርግው በሥራ ወዳድነታቸው ለሀገራቸውና ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ በተ ክርስቲያንናቸው ታሪክ፣ እምነትና ባህል የላቀ ፍቅርና እንዲሁም እውቀት የነበራቸው መሆኑ ያዘጋጇዋቸው ልዩ ልዩ ጽሑፎች ሁሉ ያረጋግጣሉ። ይህም ለአዲሱ ትውልድ አርአያነት ያለው በመሆኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስለሳቸውና እሳቸውን ስለመሳሰሉ ኢትዮጵያውያን ምሁራን በየጊዜው አውደ ጥናቶችን እያዘጋጀ ቢያስታውስ በወጣቱ ትውልድ ዘንድ ለታሪካችን ለባህላችንና ለእምነታችን ፍቅር ዕድገትና መጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ።

ፕሮፌሰር ሥርግው ዛሬ ለማንም የማይቀረውን የሞት ጽዋ ፉንታቸውን የተቀበሉ ቢሆንም ትዝታቸው ከልቤ አይጠፋም። ትዝታ ስል በቃላት ሊገለጽ የማይችለውንና የጊዜ ብዛት የማያደበዝዘውን ጣፋጭ የስሜት ትውስታ ስለምትወዱት መምህር የሚሰማችሁን የትዝታ ዓይነት ማለቴ ነው።

በመጨረሻም ስለፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ እንደተማሪያቸው ያለኝን ትዝታ እንድገልጽ እድል ለሰጡኝ ቤተሰቦቻቸውና የቅርብ ወዳጆቻቸው ጥልቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ለቤተሰቦቻቸውና ለወዳጆቻቸው በሙሉ እግዜአብሔር መጽናናት እንዲሰጣቸው፣ የፕሮፌሰርንም ነፍስ በአብራሃም፣ በይስሐቅ፣ በያዕቆብና በጻድቃን ጐን እንዲያስቀምጥልን አምላካችንን በጸሎት እንለምነው።

አቶ እሱባለው ወልደ ሥላሴ
ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የቀድሞ ተማሪያቸው
የፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ የሰማንያ ቀን መታሰቢያ
ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል
አዲስ አበባ
መጋቢት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ. ም.